# የተቃውሞ ቁም ሰልፍ ለንደን ከተማ በሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ ፊት ለፊት ተደረገ

ዛሬ፣ ህዳር 18 ቀን 2003 ዓ. ም. ከቀኑ 9 ሰዓት ጀምሮ የተቃውሞ ቁም ሰልፍ ለንደን ከተማ በሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ ፊት ለፊት ተደርጓል።

በለንደን የሚገኙ ኢትዮጵያዊ የአንድነትና የዴሞክራሲ ሃይሎች ይህንኑ የተቃውሞ ሰልፍ ያዘጋጁት ብአዴን ተብዬውን የወያኔ ተለጣፊ አሻንጉሊት ድርጅት 30ኛ ዓመት ለማክበር በሚል በኢትዮጵያ ያለው ጸረ-አንድነት እና ጸረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ ግንባር ደም ተዋንያን በረከት ስምዖንና ህላዌ ዮሴፍ በከተማው መገኘታቸውን ለመቃወም እና በሀገራችን የተካሄደውንና እየተካሄደ ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰት ለማጋለጥ ነው።

ብዛት ያላቸው በከተማውና ባካባቢው የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የዕለቱ ሃይለኛ ብርድ ሳይበግራቸው ለአራት ሰዓት ባካሄዱት በዚህ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ይስተጋቡ ከነበሩት መፈክሮች ውስጥ፡

በረከትና የብአዴን ተከታዮቹ ለፍርድ ይቅረቡ!

የብአዴን ወንጀለኞች ለፍርድ ይቅረቡ!

ወያኔ ገዳይ ነው!

ከወያኔ ዱሮ፣ የነፃነት ሽሮ! የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል። ከ15 ዓመታት በላይ በወያኔ የድብቅ እስር ቤቶች ታስረው መዳረሻቸው የጠፋው የነጸጋዬ ደብተራውና አበራሽ በርታ ፎቶዎችም ተይዘው ነበር። በሰልፉ ለተሳተፈው ሕዝብም፡

- የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ማዕከል ያደረገ፣
- ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የሚታገል፣
- አባላቱ የድርጅትን መሰረታዊ መስፈርቶች ያሚሉ

ሕብረት በኢትዮጵያዊያን ሃይሎች መካከል ሊፈጠር እንደሚገባ የሚያትተውና "የጋራ ራዕይ የሌለው ተቃዋሚ፣ የአምባገነን ሥርዓት ሰለባ ሆኖ ይቀራል" የሚለው የትዝብት አድማስ፣ ቁጥር 99 ጽሁፍ የተሰራጨ ሲሆን፣

እንዲሁም የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት በቅርቡ "ሠማዕታት ሲታሰቡ፣ የወንድም እህቶቻችንን ደም እንፋረዳለን" በሚል ርዕስ ያወጣው መግለጫ በድርጅቱ ደጋፊዎች አማካኝነት ለተሳታፊዎቹ ተሰጥቷል ። በብሪታንያ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (በእንግሊዝኛ ምህፃረ ቃል ሶሴፓ) ድጋፍ ኮሚቴ ያዘጋጀው መግለጫም በአካባቢው ለሚተላለፉ የሀገሬውና ሌሎች ሰዎች ታድሏል። ባለፈው ሳምንት ልደቱ (ክህደቱ) ጠርቶት የነበረው ስብሰባ ላይ ያጋጠመው ከፍተኛ ተቃውሞም ውጤታማ ሆኖ የወያኔ ነፍሰ-ገዳዮች በረከትና ህላዌ ወደተገኙበት ድግስ ብዙም ሰዎች ሲገቡ አልተስተዋለም።